# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 284 ጥቅምት 8 2006 ገጽ 1

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ:- ነጻነት የናፈቀህ፣ አጎንብሶና በገዛ ሀገርህ ተዋርዶ መኖር የሰለቸህ፣ በወያኔ ተሰደህ በባእድ ሀገር የምትሰቃይ፣ የምትሞት የኢትዮጵያ ልጅ ሁሉ ወያኔዎች ከግፍ አልፈው ሊቀልዱብህ፣ በቁምህ ሊገሉህ፣ ሊከፋፍሉህ አይገባም። ወያኔ የፈሪ አብራሪ ነው። አሻፈረኝ ሲሉት እንጂ ቢሸሹለት በቃኝ ብሎ አይመለስም፡፡

ግንቦት 7 ንቅናቄ እንደሁልግዜው ዛሬም ወገን ሆይ:- የሀገርህን ህልውና ለመታደግ ተነሳ፣ ተቀላቀለን፤ የመከራችንን ቀን አጭር እንደርገው ዘንድ ጻሃይ ሳትገባብን፣ ሳይመሽብን ኑ ተቀላቀሉን የሚለውን ጥሪ ዛሬም አጠናክሮ ያቀርብልሃል። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ኃ/ማሪያም ደሳለኝ “መንግስት ፈርቷል እያላችሁ ራሳችሁን አታሞኙ” ሲል ማሾፉ ተሰማ

ባለፉት ሁለትና ሦስት ሳምንታት አንዴ “ቀይ መስመር ረገጣችሁ” አንዴ ሰላማዊ ሰልፍ እከለክላለሁ፤ ሌላ ግዜ ደግሞ ኢህአዴግ ለተቃዋሚዎች ጥያቄ መልስ ሰጥቷል እያለ የባጥ የቆጡን ሲቀባጥር የሰነበተዉ የወያኔዉ ሎሌ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በዚህ ሳምንት ደግሞ በተወካዮች ምክር ቤት ተገኝቶ ““መንግስት ፈርቷል እያላችሁ ራሳችሁን አታሞኙ” ብሎ በመደንፋት “ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም” የሚባለዉን የአገራችንን ተረት የሚያስታዉስ የፈሪ ንግግር አድርጓል። ጠ/ሚኒስቴር ተብዬዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ከዚያ እንቅልፋም ፓርላማ አባላት ለቀረቡለት ጥያቄዎች መልስ ሲሰጥ መንግስት የጎዳና ላይ ነውጥ ከሚያሰቡት ሀይሎች ጋር ለመነጋገር የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል ብሏል። ከተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ጋር እንኳን መነጋገር እነሱ ባለፉበት መንገድ ማለፍ የሚፈራዉ ኃ/ማሪያም የጎዳና ላይ ነውጥ ከሚያሰቡት ሀይሎች ጋር ካሁን በኋላ አንነጋገርም ማለቱ አንዳንዶችን ያስገረመ ቢሆንም ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች አባባሉን የተለመደ የወያኔ የቃላት ጨዋታ ነዉ ብለዉ የኃይለማሪያምን ንግግር አጣጥለዉታል።

በተቃዋሚዎች ፓርቲዎች በኩል የሚቀርበው ጥያቄ ሁሉ ቅጥ ያጣ ፍረጃና የጥላቻ ፖለቲካ ብቻ ነዉ ያለዉ ሎሌዉ ሀይለማርያም ደሳለኝ የጎዳና ላይ ነውጥ እናደርጋለን ብለዉ የሚያስቡ ሀይሎች ሀሳባቸውን እንዲያቆሙ ጠይቋል። በመቀጠልም የጎዳና ላይ ነውጥ ለማስነሳት ስለሚያስቡ ኃይሎች በቂ መረጃ አለን ስንል “መንግስት ፈርቶ ማስፈራራት ጀመረ” እንባላለን ሆኖም ይህ መንግስት አይፈራም፣ ታሪኩም ባህሪውም እንደዛ አይደለም በማለት የሚያዉቀዉን የኢትዮጵያዉያንን የጀግንነትና የአይበገሬነት ታሪክ ትቶ የማያዉቀዉን፤ የሌለዉንና በታሪክ ያልተመዘገበዉን የወያኔን አለመፍራት “ይህ መንግስት ፈርቷል እያላችሁ እራሳችሁን አታሞኙ፣ መንግስት አይፈራም የህዝብ መንግስት ነው" እያለ ያለ ሀፍረት ተናግሯል። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ወይ እሱ እራሱ አይጫወትበት ወይ ሌሎቹን አያጫዉት ብቻዉን ጨምድዶ የያዘዉን ኳስ የወያኔዉ ተላላኪ ኃ/ማሪያም ጌቶቹ ሄደህ ተናገር ያሉትን ትእዛዝ ለመፈጸም ብቻ ሲል ብቻ “ኳሱ እናንተ እጅ ላይ ነው” በማለት አባባሉን እንኳን በዉል ያልተረዳዉን ምሳሌ ተናግራል።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን አባቶች መንግስት ቤ/ክርስቲያኑቱን ለማፍረስ ተነስቷል ሲሉ ከሰሱ

ወያኔ በሐይማኖት ተቋማት ላይ የሚያደርሰዉ በደልና ጫና የሰለቻቸዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርሲቲያን አባቶች የወያኔ አገዛዝ ታሪካዊቷን ቤተክርቲያን ታሪክ አልባ ለማድረግና ለማፍረስ ቆርጦ ተነስቷል ብለዉ መናገራቸዉንና ንግግሩ የአገዛዙን ባለስልጣኖች እንዳስደነገጠ ከአዲስ አበባ የደረስን ዜና አስረዳ። አባቶቹ ይህንን በቤተክርስቲያኒቱ የሺ አመታት ታሪክ ዉስጥ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነዉን በስልጣን ላይ ያለ መንግስትን ፊት ለፊት የመቃወምና የማዉገዝ ንግግር ያሰሙት ሰሞኑን አዲስ አበባ አራት ኪሎ ዉስጥ በሚገኘው መንበረ ፓትሪያርክ የስብሰባ አዳራሽ ዉስጥ በመካሄድ ላይ ባለው 32ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ነዉ። አንድ በስብሰባው ላይ የተሳተፉ አባት ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ እንደገለጹት በስብሰባው ላይ ይህ መንግስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ለማፍረስ እንደተነሳ በተደጋጋሚ ተነግሯል። እኚሁ አባት ጨምረዉ እንደገለጹት በዕለቱ በተደረገዉ ስብሰባ የፌደራል ጉዳዮች የሀይማኖት ክፍል ሃላፊዎች ስለ አክራሪነትና ጽንፈኝነት ገለጻ ለመስጠት የመጡ የአገዛዙ ካድሬዎች ተገኝተዉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

በወያኔ ዘመን ኢትዮጵያ ዉስጥ በክርስቲያን ተቋሞችና በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰዉ ግፍና መከራ እየጨመረ መምጣቱን አባቶቹ ተራ በተራ የተናገሩ ሲሆን ፓትሪያሪኩም አባቶች የተናገሩትን በመደገፍ እውነት ነው ይህ ሁሉ መከራና ጫና አለብን በማለት በሊቀ ጳጳሳቱ የተነገረውን ሀሳብ ደግፈዋል። ከመላው አለም የተሰባሰቡ በሺዎች የሚቆጠሩ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ስብሐት ነጋና አሜሪካ የሚኖረዉ አግአዚ ኢትዮጵያዊዉን ደብድበዉ ተሰወሩ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት አይኑ አይቶ ያልወደደዉን ሁሉ እንዳሰኘዉ ሲያስር፤ ሲደበድብና ሲገድል የኖረዉ ወንጀለኛዉ ሽማግሌ ስብሐት ነጋ ያንን የለመደዉን ወንጀል አሜሪካ ድረስ ይዞ በመምጣት እየተከተለዉ ቪድዮ ሲቀርጸዉ የነበረዉን አንድ ወጣት ኢትዮጵያዊ ከአጃቢዉ ጋር ደብድቦ መሰወሩን አሜሪካ ግዛት ቨርጂኒያ ዉስጥ የሚገኙ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ከአሜሪካዋ መናገሻ ከዋሺንግተን ዲሲ በስተደቡብ አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ወጣ ብላ በምትገኘዉ አሌክሳንደሪያ ቨርጂኒያ ዉስጥ ነበር ስብሐት ነጋና እዚሁ ዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ የሚኖረዉ ታምራት ገ/መድህን የተባለ የህወሃት ሰላይ መስፍን ወርቅነህ የተባለዉን ሰላማዊ ኢትዮጵያዊ ለምን ቪድዮ ትቀርጻናለህ ብለዉ ያለበት ቦታ ድረስ ሄደዉ የደበደቡት። ተደብዳቢዉ መስፍን ወርቅነህ የተባለዉ ወጣት ጉዳት ደርሶበት እዚያዉ አለክሳንደሪያ ዉስጥ ወደሚገኘዉ ሆስፒታል ተወስዶ የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና ዕርዳታ የተደረገለት ሲሆን የድብደባዉን ዜና የሰማዉ የአሌክሳንደሪያ ከተማ ፖሊስ ወንጀሉ ወደተፈጸመበት ቦታ ደርሶ ተጠርጣሪዎቹን ቢፈልግም ወንጀሉን የፈጸሙት ስብሐት ነጋና አጃቢዉ ታምራት ገ/መድህን ለግዜዉ ከፖሊስ መሰወራቸዉ ታዉቋል። የድብደባዉን ዜና ከኢሳትና ከሌሎች የተለያዩ የአካባቢዉ የዜና ማሰራጫዎች የሰሙት ኢትዮጵያዉያን የህግ ባለሙያዎችና የሲቪክ ማህበረት መሪዎች በስብሐት ነጋና በአጃቢዉ ላይ ክስ መስርተዉ ጉዳዩ በፖሊስ በመጣራት ላይ ነዉ። ይህ በዚህ እንዳለ የአሌክንደሪያ ፖሊሶች የነስብሐት ነጋ ጥቃት ሰለባ የሆነዉን መስፍን ወርቅነህን ድብደባዉን አስመልክቶ አነጋግረዉ የምስክርነት ቃሉን ተቀብለዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አዲስ አበባ ዉስጥ ቦምብ ፈንድቶ የሁለት ሰዎች ህይወት አጠፋ

አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ዉስጥ በተለምዶ ሩዋንዳ ማዞሪያ እየተባለ በሚጠራዉ አካባቢ ባለፈዉ እሁድ ጥቅምት ሦስት ቀን 2006 ዓም ቦምብ ፈንድቶ ሁለት ሰዎች መሞታቸዉን ተገለጸ። ከፌዴራል ፖሊስ የፀረ ሽብር ግብረ ኃይል በተገኘዉ መረጃ መሰረት በቦምቡ ፍንዳታ ሕይወታቸው ያለፈው ሁለቱ ሰዎች በህገወጥ መንገድ ወደ አገር ዉስጥ የገቡ የሶማሌ ዜጎች ሲሆኑ እንደ ፌዴራል ፖሊስ አገላለጽ ፍንዳታዉ የደረሰዉ ሰዎቹ ቦምቡን በሰዉነታቸዉ ዉስጥ ደብቀዉ ወደ ዕላማቸዉ ለመሄድ ሲዘጋጁ ነዉ። ፌዴራል ፖሊስ የሰጠዉን መግለጫ አስመልክቶ ከገለልተኛ አካላት የተሰጠ ሌላ መግለጫ ባይኖርም የሁለቱ ሰዎች ዝግጅትና ለመመሳሰል ብለዉ የያዙት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን መለያ እንደሚያመለክተዉ የሁለቱ ሰዎች የጥቃት ተልዕኮ አዲስ አበባ ስቴድዮም ሳይሆን እንዳልቀረ ተገምቷል። ጥቅምት ሦስት ቀን የኢትዮጵያና ናይጀሪያ ቡድኖች ለአለም ዋንጫ ማጣሪያ የተጫወቱበት ቀን ስለነበር አዲስ አበባ ስቴድዮምና አካባቢዉ በዕለቱ በብዙ ሺዎች በሚቀጠሩ የስፖርት አፍቃሪዎች ተጨናንቆ እንደነበር የሚታወስ ነዉ።

የአልሸባብ ሽብርተኞች እንደሆኑ የሚነገረዉ ሁለቱ የሶማሌ ዜጎች እጃቸዉ ላይ ከፈነዳዉ ቦምብ በተጨማሪ መጠናቸው ያልተገለጸ ቦምቦችና አንድ ሽጉጥ ከሁለት ካርታ ጥይት ጋር፣ የፈንጂ ማቆጣጠያና የአደጋ መከላከያ ጃኬቶች፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ማሊያና ቀበቶዎች መገኘታቸውም ተገልጿል፡፡ የአንድ ግለሰብ ሰርቪስ ቤት ተከራይተው ከነበሩት ሁለቱ የሶማሌ ዜጎች ዉስጥ አንደኛው ከ20 ቀናት በላይ የቆየ ሲሆን፣ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ኃ/ማርያም ደሳለኝ ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ አፍሪካን እንዳይዳኝ ለማድረግ እየተሯሯጠ መሆኑ ታወቀ

የወያኔዉ ጠ/ሚኒስቴርኃ/ማርያም ደሳለኝ ከጌቶቹ በተሰጠዉ መመሪያ መሰረት የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙትን የወያኔ መሪዎች ከተጠያቂነት ለማዳን ቀንና ማታ እየሰራ መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ዘጋቢዎቻችን ዲፕሎማቲክ ምንጮችን በመጠቀስ በላኩልን ዜና ገለጹ። በኬንያ አነሳሽነት የአፍሪካ ኅብረት በቅርቡ በአዲስ አበባ ዉስጥ በጠራዉ አስቸኳይ ስብሰባ ላይ የወቅቱ የኅብረቱ ሊቀ መንበር የሆነዉ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ፣ የአለም አቀፉን የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ‹‹የአፍሪካ መሪዎችን አዳኝ ተቋም›› ብሎ ሲጠራዉ የተደመጠ ሲሆን ኃ/ማሪያም ከዚህ በተጨማሪ አለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በአፍሪካ ላይ በሚወስዳቸው ዕርምጃዎች የአፍሪካ ኅብረት በተደጋጋሚ ቅሬታውን ያሰማ ቢሆንም፣ አንድም ጊዜ አልተደመጠም የሚል ተልካሻ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ የአፍሪካ ህብረት በእንደዚህ አይነቱ ጉዳይ ላይ በመሪዎች ደረጃ ሲሰበሰብ የመጀመሪያ ቢሆንም የኢትዮጵያ መሪዎች ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔና አሸባሪነት ምንና ምን ናቸው

የወያኔ ጉጅሌ ሰሞኑን የሚያሳዝን ባይሆን ኖሮ በእጅጉ ሊያስቅ የሚችል ቧልት ላይ ተጠምዷል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ሳይቀር ህብረተሰቡን በየተቋሙና በየመኖሪያው እየሰበሰበ ስለሽብርተኝነት ማብራሪያና ገለፃ በመስጠት ዜማ ላይ ተጠምዷል።

የወያኔ የሽብረተኝነት ገለፃ ዘመቻ ሚስጥር ደግሞ ብዙ ምርምር የሚሻ አይደለም። የሀገራችን ሰዎች ዶሮ ጭራ ልታወጣው የምትችል የሚሉት አይነት ሚስጥር ነው። አላማው ነጻነት አማረኝ፣ እምቢ ዘረኝነት እና ቢያንስ መሰረታዊ ሰበአዊ መብቴ ይገባኛል በማለት መብቱን እየጠየቀ የመጣው ህዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ታይቶታል።

የማእበሉ የመጀመሪያ ንቅናቄዎች ከወዲያ ወዲህ መታየት ጀምረዋል። የገለፀው ሽርጉድ ዋና አላማ ይህ መብቱን የሚጠይቅና አጎንብሶ መኖር የሰለቸው ህዝብ ለመብቴ የማደርገውን ትግል ሽብርተኛ ያስብለኛል ብሎ እንዲፈራና ይበልጥ እንዲያጎነብስ መሆኑ ነው። ይህን ደግሞ ህዝቡ አውቆታል። ሰሞኑን በአለምያ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ለገለፃው ለመጡ ካድሬዎች የሰጧቸው አጸፋዊ ገለጻ ይህንኑ ያሳያል፡፡

ሽብርተኝነት አንድና በነጻነትና በዴሞክራሲ ለመኖር የሚመኝና የወሰነን ህዝብ ሰላም በመንሳት የፖለቲካ አላማዬን አሳካለሁ ብለው የሚያምኑ ቡድኖችና ድርጅቶች የፖለቲካ መሳሪያ ነው። የወያኔ መሪዎች የሽብርተኝነት ትርጉም አልገባቸው ከሆነ ሰብስብ ብለው መሰዋእት ፊት ቢቆሙ ሽብረተኝነትን አፍጥጦ ሊያዩት ይችላሉ፡፡ ሽብርተኛው ወያኔና ወያኔ ብቻ ነው።

ህዝቡ ፊት በቆሙ ቁጥር ግን ህዝቡ ሽብርተኞችን ያያል። ሰለባውን ለማስተማር መሞከር ለእናት ምጥ የማስተማር ያህል ነው፡፡ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉንም የዴሞክራሲና የሰላም ጥያቄ ሁሉ በጉልበትና ባፈና የደፈጠጠ አሸባሪ ቁጥር አንድ ወያኔ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ከሽብር ጋር የመረረ ችግር ላለባቸው ሀገሮች ሎሌነት ገብቶ ሌሎች ሽብርተኞችን ወደሀገራችን የሚጎትተው ራሱ ወያኔ ነው።

ዛሬ በማንም የባእድ አሸባሪ በህዝባችን ላይ ለሚደርስ ጉዳት ዋናው ተጠያቂ ወያኔ የሚሆነውም ለዚህ ነው። ለምእራብያውያን ጻረ ሽብር አጋራችሁ ነኝ እያልኩ ራሴ በምገዛው ህዝብ ላይ የምፈጽመውን ሽብር እንዳለ ያዩልኛል፣ ፍርፋሬም አገኝበታለሁ በሚል ስሌት የተገባበት መሆኑንም የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ ትንሽ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፡- ነጻነት የናፈቀህ፣ አጎንብሶና በገዛ ሀገርህ ተዋርዶ መኖር የሰለቸህ፣ በወያኔ ተሰደህ በባእድ ሀገር የምትሰቃይ፣ የምትሞት የኢትዮጵያ ልጅ ሁሉ ወያኔዎች ከግፍ አልፈው ሊቀልዱብህ፣ በቁምህ ሊገሉህ፣ ሊከፋፍሉህ አይገባም። ወያኔ የፈሪ አብራሪ ነው። አሻፈረኝ ሲሉት እንጂ ቢሸሹለት በቃኝ ብሎ አይመለስም፡፡

ግንቦት 7 ንቅናቄ እንደሁልግዜው ዛሬም ወገን ሆይ፡- የሀገርህን ህልውና ለመታደግ ተነሳ፣ ተቀላቀለን፤ የመከራችንን ቀን አጭር እንደርገው ዘንድ ጻሃይ ሳትገባብን፣ ሳይመሽብን ኑ ተቀላቀሉን የሚለውን ጥሪ ዛሬም አጠናክሮ ያቀርብልሃል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን አባቶች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሀይማኖቱ መሪዎች በተገኙበት ስብሰባ ላይ የተገኙት የመንግስት ባለስልጣናት የኢትዮጵያን የሀይማኖት ታሪክ አሳንሰዉና አጣጥለዉ ሲያቅርቡ ያዳመጡት አባቶች በቁጣ በመነሳት ለወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ተገቢዉን ምላሽ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያን ህዝብ መሬት ነጥቃችሁ፣ ህዝቡንም መሬቱንም የመንግስት ያደረጋችሁት እናንተ ናችሁ፣ ኢትዮጵያዊው ሀብትና ንብረት እንዳይኖረው ያደረጋችሁትም እናንተዉ ናችሁ። የኢትዮጵያን ህዝብ ከዚህ ቀደም የነበሩት መንግስታት ካደረሱበት የበለጠ መከራና ስቃይ ያየዉ በዚህ መንግስት ግዜ ነዉ በማለት አባቶቹ የወያኔን ባለስልጣናት ግራ በጋባና ባስደነገጠ መልኩ ትችትና ወቀሳ አቅርበዋል። ከስብሰባዉ ተካፋዮች አንዱ የሆኑት ብጹዕ አቡነ ቄርሎስ "በአጼዎቹ ዘመን አገራችን ታሪኳ የተከበረ ነበር፤ እናንተም ይህችን አገር ስትረከቡ እስከ ታሪኩዋ ነው . . . ታሪኩዋን አላጠፋችሁም ወይ?" ብለዉ ሲጠይቁ አዳራሹ ዉስጥ የነበረዉ ሰዉ ሁሉ አድናቆቱን በጭብጨባ ገልጾላቸዋል። በዕለቱ ስብሰባ ላይ የተሳተፉት አብዛኛዎቹ የሀይማኖት አባቶች የቤተክስርቲያኗን ታሪክ አዛብታችሁዋል፣ ቤተክርስቲያኑዋንም ታሪኩዋን አጥፍታችሁዋል በማለት ባለስልጣናቱን ወጥረው መያዛቸው ታውቋል። በስብሰባዉ ላይ የሰሜን ወሎ አገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ብጹዕ አቡነ ቄርሊዮስ፣ የምእራብ ወለጋ አገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ብጹዕ አቡነ ሄኖክ፣ የጋሞ ጎፋ አገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ብጹዕ አቡነ ኤሊያስ፣ የምስራቅ ጎጃም ሊቀ ጳጳስ ብጹ አቡነ ማርቆስና የደቡብ ጎንደር ሊቀጳጳስ ብጹዕ አቡነ እንድሪያስ ተገኝተዋል።

---

## ስብሐት ነጋና አሜሪካ የሚኖረዉ አግአዚ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የስብሐት ነጋና የአጃቢዉ የታምራት ገ/መድህን ድፍረት ዲሲ፤ ቨርጂኒያና ሜሪላንድ ግዛቶች ዉስጥ የሚኖረዉን ኢትዮጵያዊ ያስቆጣ ሲሆን ኢትዮጵያዊያኑ ፖሊስና ፍርድ ቤት በሁለቱ ወንጀለኞች ላይ የሚወስዱትን እርምጃ ለማወቅ በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ናቸዉ። የዚህ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያናገራቸዉ አንድ በቅርቡ ከኢትዮጵያ የመጡ ታደለ ጉርሙ የተባሉ ግለሰብ "የእነሱን ድብደባና እርግጫ ላለማየት አገሬን ጥዬ መጣሁ እነዚህ አይነ ደረቆች እዚህም እያመጡ ሰዉ ይደበድባሉ እንዴ" ካሉ በኋላ ደግነቱ አገሩ አሜሪካ ነዉና ሌላ ቢቀር እኛን አገራችን ዉስጥ የነፈጉንን ፍትህ እነሱ እዚህ በአይናቸዉ ያያሉ ብለዋል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ በመካሄድ ላይ ያለዉ ህዝባዊ እንቅስቃሴ መጎልበት፤ የተቃዋሚ ኃይሎች ጡንቻ መፈርጠምና የቱባ ቱባ የህወሃት ባለስልጣኖች አገር ጥሎ መፈርጠጥ ያሳሰባቸዉ የወያኔ ሹማምንት በትዕቢተኛዉ መሪያቸዉ በስብሐት ነጋ መሪነት እዚህ አሜሪካ መጥተዉ ከአሜሪካ መንግስት ባለስልኖች፤ እግሬ አዉጭኝ ብለዉ ከፈረጠጡ አባላቶቻቸዉና ከጥቂት ሆዳም ደጋፊዎቻቸዉ ጋር በመነጋገር ላይ መሆናቸዉ በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች መዘገቡ የሚታወስ ነዉ። ትላልቅ የአገዛዙን የደህንነት ባለስልጣኖች ጨምሮ ከፍተኛ የህወሃት መሪዎችን ይዞ አሜሪካ የገባዉ የወያኔ ቡድን አሜሪካ ደርሶ እንቅስቃሴዉን እስኪጀምር ድረስ ትግርኛ ተናጋሪ ከሆኑት የኤምባሰዉ ሰራተኞች ዉጭ ግርማ ብሩን ጨምሮ ሌሎቹ ከፍተኛ የኤምባሲዉ ባለስልጣኖች በፍጹም አለመስማታቸዉን ከዉስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘዉ መረጃ ያለመክታል። ከፍተኛ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት አሜሪካ ሲመጡ አሜሪካ ዉስጥ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ አምባሳደር አለማዉቁ የሚያሳየዉ አስፈላጊ በሆኑ የኢትዮጵያ ጉዳዮች ወያኔ ከትግርኛ ተናጋሪዎች ዉጭ ማንንም የማያምን ዘረኛ ድርጅት መሆኑን ነዉ ሲሉ ብዙዎች ትችት ይሰነዝራሉ።

---

## ኃ/ማርያም ደሳለኝ ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አለም አቀፉን የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ሲያወግዙ ግን ኃ./ማሪያም ደሳለኝ የመጀመሪያ አይደለም። የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኦማር አል በሽር ባለበት ቦታ እጁ ተይዞ ለአለም አቀፉ ፍርድ ቤት እንዳይሰጥ ከፍተኛ ተጋድሎ ማድረጉ የሚታወስ ነዉ።

የአይጥ ምስክር ድንብጥ እንዲሉ የወቅቱ የአፍሪካ ኅብረት የአስፈጻሚ ምክር ቤት ሊቀመንበር የሆነዉ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም ‹‹የፀጥታው ምክር ቤትና ፍርድ ቤቱ በተከተሉት 'ደብል ስታንዳርድ' ምክንያት ኅብረቱ ያቀረባቸውን ቅሬታዎች 'ጆሮ ዳባ ልበስ' ብለውታል ሲል ተደምጧል፡፡ ቀጥሎም የራሱ ፓርቲ አባል የነበዉና የትግል ጓደኛዉ መለስ ዜናዊ አይኑ ፊት የአኘዋክን ህዝብ ሲጨፈጭፍ ዝም ብሎ የተመለከተዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም "ዜጐቻቸውን የሚጨፈጭፉ የአፍሪካ መሪዎችን ተቀምጠን አናይም" ብሏል፡፡ "ድምፃችን ከፍ ብሎ መሰማት መጀመር አለበት" በሚል ኃይለቃል ንግግሩን ያጠቃለለዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም፣ የአፍሪካ ኅብረት አባል አገር መሪ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቱ መጠየቅ ፍፁም ንቀት መሆኑን ተናግሯል፡፡ ኃይለማሪያምና ቴዎድሮስ አድህኖም "እንዳሰኘን መግደል ይፈቀድልን" የሚል አስቀያሚ ዘመቻ መጀበሩበት በአሁኑ ወቅት አፍሪካን ከአለም አቀፉ የወንጀለኞቸ ፍርድ ቤት ለመነጠል የሚደረገዉን ጥረት አምርረዉ የሚቃወሙ አገሮች፤ ምሁራንና ተደማጭነት ያላቸዉ ታላላቅ ሰዎች በየቦታዉ ብቅ ማለት ጀምረዋል። ከእነዚህም መካከል የቀድሞዉ የተመድ ዋና ጸሐፊ ጋናዊዉ ኮፊ አናንና የኖቤል ሰላም ሽልማት ተሸላሚ የሆኑት ደቡብ አፍሪካዊዉ ዴዝሞንድ ቱቱ ይገኙበታል፡፡ ጋናዊዉ ኮፊ አናን የአፍሪካ መሪዎች እራሳቸዉን ከአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለማግለል የሚያደርጉትን ጥረት "የኃፍረት ባጅ" ማንጠልጠል ነዉ ብለውታል፡፡ የኖቤል የዓለም የሰላም ተሸላሚው ሊቀ ጳጳስ ዴዝሞንድ ቱቱ ደግሞ "ፍርድ ቤቱን ዋጋ ቢስ" ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ አነ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን የመሳሰሉ መሪዎች ሕዝባቸውን ለመግደል፣ ለማሰቃየትና ለመጨቆን ፈቃድ እየጠየቁ እንደሆነ ነው የምቆጠረው ብለዋል፡፡

---

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# የሞኝ ዘፈን አሁንም አሁንም አበብዬ

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ከዚህ ቀደም በቁንጨቸዉ በመለስ ዜናዊ በኩል እንኮረኩማለን፤ ምላስ እንቆርጣልን ወይም እጅ እናስራለን እያሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስተላልፉ የነበረዉን የማስፈራሪያ ቃላት ጋጋታ ባለፈዉ ዐርብ መስከረም 26 ቀን ለዚሁ እኩይ ተግባራቸዉ በቀጠሩት ታማኝ ሎሌያቸዉ በኃ/ማሪያም ደሳለኝ በኩል ሲያስተላልፉ ተደምጠዋል። እንዳሰለጠኑት ጌኛ ፈረስ ወያኔ ባሳየዉ አቅጣጫ ሽምጥ የሚጋልበዉና ከጭንቅላቱ ወጥቶ የሚነገር ምንም ነገር የሌለዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝም የአሜሪካዉን ፕሬዚዳንት የባራክ ኦባማን አባባል እንዳለ በግርድፉ ወስዶ "ከቀይ መስመር በላይ መሄድ የሚፈልግ ይቆነጠጣል" ሲል በዚያ ባልተቆነጠጠ አፉ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ደንፍቷል። የወያኔዉ ተላላኪ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ አልገባዉም እንጂ ይህ ቀይ መስመር ታልፉና ወዮላችሁ የሚሉት ዛቻ አንኳን በአንድ ጀምበር ትርምስምሱ ሊወጣ በሚችል የጦር ኃይል ለሚተማመነዉ ወያኔን ለመሰለ ፀረ ህዝብ ኃይል ቀርቶ በህዝብ ሙሉ ፈቃድ የተመረጠዉና የአለማችንን አስፈሪና እጅግ ጠንካራ ጦር የሚመራዉ ባራክ ኦባም ከተናገረና ከዛተ በኋላ ዛቻዉ አላዋጣ ስላለዉ ሌሎች አማራጮችን ለመመልከት ተገድዷል።

ባለፈዉ ዐርብ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የተናገራቸዉን ተራ ንግግሮች ሁሉ እንመልከት ብንል እንደሱ ስራ ፈቶች አይደለንምና ግዜዉም ፍላጎቱም የለንም፤ ሆኖም አንዳንድ ንግግሮቹ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ የሚያደርገዉን ትግል በንቀት አይን የተመለከቱ ናቸዉና ግንቦት 7 የሚያካሄደዉ የነጻነት ትግል ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ከወያኔ ባርነት ነጻ ማዉጣትንም ያጠቃልላልና ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ይህንን ምክር አዘል መልዕክታችንን እንዲያዳምጥ እንጋብዘዋለን። ደግሞም የግንቦት ሰባትን እንቅስቃሴ እከታተላለሁ ብሎ ሲናገር ከራሱ አንደበት ሰምተናልና ምክራችንን ይሰማል የሚል ሙሉ እምነት አለን።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ አገር ዉስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያነሷቸዉን ጥያቄዎች አስመልክቶ ከጋዜጠኞች የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ ኢትዮጲያ ዉስጥ ወደ ዘጠና የሚጠጉ ፓርቲዎች ስላሉ ዘጠና እሁዶችን መጠበቅ አለብን በማለት ከተጠየቀዉ ጥያቄ ጋር በፍጹም የማይገናኝና እንኳን ከአገር መሪ ከሦስተኛ ክፍል ተማሪም የማይጠበቅ ተራ መልስ መልሷል። ከዚህ በተጨማሪ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እሁድ እሁድ በሚያደርጓቸው ሰላማዊ ሠልፎች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተመሳሳይ ስለሆነ መንግሥት ምን ምላሽ መስጠት እንዳለበት ሊገባው አልቻለም በማለት ኃ/ማሪያም የእሱን የራሱን ብቻ ሳይሆን እሱ የሚመራዉ መንግስትም ምን ያክል ጨቅላ መንግስት እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል። የኃ/ማሪያምና የጌቶቹ ጨቅላነትና ባዶነት ደግሞ አገር ያወቀዉና ፀሐይ የሞቀዉ እዉነት ነዉና ብዙ መረጃ የሚያስፈልገዉ አይመሰለንም። ከሰሞኑ አማካሪ ተብለዉ ኃ/ማሪያምን የከበቡትን ሰዎች መመልከቱ ይበቃል። የጭንቅላቱ ዝገት ለይቶለት በመለስ ዜናዊ ግዜ ስኳር እንዲቅም መተኃራና ወንጂ የተላከዉ አባይ ፀሐዬ እሱ እራሱ ይመረመር እንደሆነ ነዉ እንጂ አባይ ፀሐዬ እንኳን ለፖሊሲ ምርምር የተመራማሪዎችን ዶሴ ለመሸከም የማይበቃ ሰዉ ነዉ . . . ችግሩ "ግም ለግም አብረህ አዝግም" ነዉና ከምሁርና ከአዋቂ ጋር የተጣሉት የወያኔ መሪዎች አንዱን ጅል የሌላዉ ጅል አማካሪ እያደረጉ የፈረደባትን አራት ኪሎን የጅሎች መንደር አደረጓት።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ባለፈዉ ዐርብ ከአንድ ሰዐት በላይ በፈጀዉ ጋዜጣዊ መግለጫዉ ወቅት የተናገረዉ አንድ ብቸኛ እዉነት ቢኖር "መንግስት ተቃዋሚዎች ለሚያቀርቡት ጥያቄ ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለበት ሊገባዉ አልቻለም ብሎ የተናገረዉ ንግግር ብቻ ነዉ። አዎ በተራ የመንገድ ላይ ፖለቲከኞችና ዘራፊዎች የሚመራዉ የወያኔ /ኢህአዴግ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚቀርብለትን የመብትና የነጻነት ጥያቄ ቀርቶ በአገዛዙ በራሱ መሃል የሚነሱ ጥያቄዎችን በቅጡ ተረድቶ የመወያየት ብቃትም ችሎታም ያለዉ አገዛዝ አይደለም። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በአንድ በኩል ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለህዝብ ማለት የፈለጉትን ብለዋል፤ ህዝብም በሚገባ ሰምቷቸዋል በማለት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚዎች ለጠየቁት ጥያቄ መንግስት ተገቢዉን ምላሽ ሰጥቷል አሁን እየጠየቁ ያሉት ተመሳሳይ ጥያቄ ነዉ በማለት እሱም ሆነ ፈላጭ ቆራጩ የወያኔ አገዛዝ እንመራለን የሚሉትን ህዝብ የፖለቲካ ምጥቀት በፍጹም የማይመጥኑና ቀድሟቸዉ የሄደዉን ህዝብ ከኋላ ሆነዉ የሚመሩ ኋላ ቀሮች መሆናቸዉን በግልጽ አሳይቷል። ኃ/ማሪያም በሰላማዊ ሰልፍና በህዝብ መካከል ያለዉ አንድነትና ልዩነት የገባዉ ሰዉ አይመስልም፤ ለዚህ ነዉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቡት ጥያቄ ለህዝቡ መስሎት ህዝብ ሰምቷቸዋል ብሎ የተናገረዉ፡፡

ኃ/ማሪያም እንደሚለዉ መንግስት የህዝብን ጥያቄ መልሶ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ከዘረኞች ተላቅቃ ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት አገር ትሆን ነበር፤ ወይም ኃ/ማሪያም እራሱ የሞተ ሰዉ ራዕይ መሸከሙን አቁሞ የራሱ ጭንቅላት ያመነጨዉንና በራሱ እይታ ያየዉን ራዕይ ያጋራን ነበር። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተደጋጋሚ ፍትህ፤ ነጻነት፤ እኩልነትና ዲሞክራሲ እያሉ የሚጮሁት እነዚህ ጥያቄዎች ካልተመለሱ በሚወክሉት ህዝብና በአገራቸዉ በኢትዮጵያ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን መጠነ ሰፊ ችግር ከወዲሁ ስለሚታያቸዉ ነዉ። እርግጠኞች ነን፤ ኃ/ማሪያም ደሳለኝም እንደ ተቃዋሚዎች አገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ነዉና ዘረኞች ያጠለቁለትን ማስክ አዉልቆ በራሱ አይን ማየት ሲጀምር እሱም እንደ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከተቃዋሚዎች ጋር ተሰልፎ ለነጻነቱ መጮህ ይምራል ብለን እናምናለን።

በእርግጥ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ከፖለቲካ ብስለቱና ካለዉ ልምድ አኳያ ሲታይ ብዙዎቹ አገር የመምራት ዉስብስብ ነገሮች ላይገቡት ይችሉ ይሆናል፤ ሆኖም ግን የአገርና የመንግስት መሪ ነኝ የሚል ሰዉ ህዝብ ላቀረበለት ጥያቄ ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ሊገባን አልቻለም ማለቱ የሚያሳየን አገራችን ኢትዮጵያ የምትመራዉ ለዕድር ዳኝነትም በማንመኛቸዉ ባዶ ሰዎች መሆኑን ነዉ። በተለይ 99.6% የህዝብ ድምጽ አገኘሁ ብሎ የሚመጻደቅ መንግስት የዚሁኑ መረጠኝ የሚለዉን ህዝብ ጥያቄ እንዴት መመለስ እንደሚገባዉ ካላወቀ ሌላ ምን ሊያዉቅ ይችላል!

ኢትዮጵያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ህዝብ የሚኖርባት ትልቅ አገር ናት፤ በእርግጥ 90 ሚሊዮን ህዝብ የሚጠይቀዉን ጥያቄ ማስተናገድ ለማንም አገር መንግስት አዳጋች ሊሆን ይችላል ፤ ነገር ግን መልስ የለንም ወይም ጥያቄዉ አልገባንም እየተባለ የህዝብ ጥያቄ ቆሻሻ ቅርጫት ዉስጥ አይጣልም ። በእርግጥ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በጠ/ሚኒስቴርነቱ ጥርስ የለሌዉ አንበሳ ነዉና የህዝብን ጥያቄ መመለስ አይችል ይሆናል፤ ሆኖም ኃ/ማሪያምን በቅርብ የሚያዉቁት ሰዎች ሐይማኖታዊ ስነምግባሩንና አንደበተ ጨዋነቱን ተመልክተዉ ሌላ ሁሉ ቢቀር በእነዚህ ሁለት ባህሪይዎቹ ብቻ የተቀመጠበትን ወንበር ይመጥናል ብለዉ ገምተዉ ነበር። ችግሩ "ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች" ነዉና ዛሬ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ አንደ ገለባ ቀልሎ የሚታየዉ በዚሁ በተነገረለት ጠንካራ ጎኑ በኩል ነዉ። ለመሆኑ መቼ ነዉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እትዮጵያ ዉስጥ በየእሁዱ ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት? ደግሞስ የወያኔ አገዛዝ ሰላማዊ ሰልፍ በተጠራ ቁጥር የሰላማዊ ሰልፉን አስተባባሪዎችና ሰልፈኛዉን የሚደበድብ ኃይል ነዉ የሚያሰማራዉ እንጂ ከመቼ ወዲህ ነዉ ወያኔ ለህዝብ ደህንነት አስቦ የጥበቃ ኃይል አሰማርቶ የሚያዉቀዉ? ካለፈዉ ግንቦት ወር ጀምሮ ሰማያዊ ፓርቲና አንድነት ፓርቲ አዲስ አበባ ዉስጥ የጠሩት ሰላማዊ ሰልፍ ሦስት ወይም አራት ቢሆን ነዉ፤ በዚህ ግዜ ዉስጥ ደግሞ ማንን እንደሚቃወም ባይታወቅም ገዢዉ ፓርቲም ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል። ታድያ የቱን ሰላማዊ ሰልፍ ነዉ ኃ/ማሪያም በየሳምንቱ የሚደረገዉ ሰላማዊ ሰልፍ ሰለቸን ብሎ የተናገረዉ? ወይስ የጌታዉን የመለስ ዜናዊን ራዕይ ከግቡ ማድረስ እንደጌታዉ መዋሸትንም ያጠቃልላል?

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎችና አንደቤት መኪናቸዉ የሚዘዉሩት ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በተፈጥሯቸዉ የህዝብ ጥያቄ የማይገባቸዉ ግዑዞች ሆነዉ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት መብቴንና ነጻነቴን አክብሩልኝ ብሎ የጠየቀዉ በየእሁዱ ብቻ ሳይሆን በየቀኑ ነዉ። ሆኖም ይህ ህዝባዊና ህጋዊ ጥያቄዉ ከወያኔ በኩል ያገኘዉ ምላሽ ድብደባ፤ እስር፤ ግድያና ስደት ብቻ ነዉ። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ሚኒልክ ቤ/መንግስት ከገባ ገና አመት ከመንፈቅ አልሞላዉም፤ ችግሩ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሚኒልክ ቤ/መንግስት የሚገቡ ሰዎች ሁሉ የሚያስቡት በጭንቅላታቸዉ ሳይሆን በጡንቻቸዉ ነዉ፤ የኃ/ማሪያም ደሳለኝ የሰሞኑ ከቀይ መስመር በላይ መሄድ ያስቆነጥጣል የሚለዉ ማስፈራርያ የሚያሳየዉ እሱም እንደ ጌቶቹ በጡንቻዉ ማሰብ መጀመሩን ነዉ። የሚገርመዉ ኃ/ማሪያም ጡንቻ ያላቸዉ ሰዎች የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነዉ እንጂ የራሱ የሆነ ጡንቻ ያለዉ ሰዉ አይደለም። ይህ ጡንቻ ቀርቶ የራሱ የሆነ ራዕይ የሌለዉ ሰዉ በስልጣን ዘመኑ አዲስ አበባ ዉስጥ ያያቸዉ ሰላማዊ ሰልፎች አምስት አይሆኑም። እንግዲህ ይታያችሁ አመት ከመንፈቅ አገር እየመራ አምስት ሰላማዊ ሰልፎች ባልተደረጉበት ከተማ ዉስጥ ነዉ በየእሁዱ የሚደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ይሰለቻሉና ለማቆም እንገደዳለን ያለዉ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ሃያ ሁለት አመት ሙሉ ጥያቄ በጠየቀ ቁጥር እየታሰረ፤ እየተደበደበና እየተገደለ ሰለቸኝ አላለም። ደግሞስ የተቃዉሞ ሰልፍ ማድረግ ህገ መንግስቱ የፈቀደዉ መብት ነዉ፤ የዲሞክራሲም አካል ነዉ እያለ ያቅራራዉ ኃ/ማሪያም ለመሆኑ እሱ እራሱ ማነዉና ነዉ ሰላማዊ ሰልፎችን ለማቆም እንገደዳለን ያለዉ?

ሌላዉ አንደ ሰነበተ የድሃ ድሪቶ እምቅ እምቅ የሚሸትተዉ የኃ/ማሪያም ንግግር የአገር ዉስጥ ተቃዋሚ ድርጅቶች ያነገቡት ጥያቄ የግንቦት 7 ጥያቄ ነዉ ብሎ የተናገረዉ እርባና ቢስ ንግግር ነዉ፤ ለመሆኑ ወያኔን የመሰለ ዜጎችን በየአደባባዩ የሚገድል ወንጀለኛ መንግስት ባለበት አገር የሚኖሩ ተቃዋሚ ድርጅቶች ምን ጎድሏቸዉ ነዉ የራሳቸዉ ያልሆነ ጥያቄ አንግበዉ የሚታገሉት? ኃ/ማሪያምም ሆነ ጌቶቹ የወያኔ ዘረኞች አንድ ሊረዱት የሚገባ ነገር ቢኖር ኢትዮጵያን ህዝብ በተመለከተ የአገር ቤትና የዉጭ አገር ወይም ህጋዊና ህጋዊ ያልሆኑ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚባል ክፍፍል የለም። ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ጥያቄያቸዉ አንድና ተመሳሳይ ነዉ፤ እሱም የህዝብ የመብትና የነጻነት ጥያቄ ይመለስ የሚል ጥያቄ ነዉ።

የአዛኝ ቅቤ አንጓቹ ኃ/ማሪያም ኬንያ ዉስጥ የደረሰዉ የሽብር ጥቃት በኢትዮጵያ ላይ እንደደረሰ ይሰማናል ብሎ ሲናገርም ተደምጧል፤ ይህ አባባል ፖለቲካ፤ ቋንቋ፤ ዘርና ሀይማኖት ሳይለይ የሁሉም ኢትዮጵያዊ እምነት ነዉ። ሆኖም የጎረቤቱ ህዝብ አደጋ ሲደርስበት ኃዘን የሚሰማዉ መሪ የራሱን አገር ህዝብ ለጦር ሜዳ በሰለጠነ ኮማንዶ አያስጨፈጭፍም። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለኬንያ ህዝብ መራራቱና ሀዘናቸዉን መጋራቱ መልካም ነዉ፤ ነገር ግን ባለፈዉ ሐምሌ ወር ኮፈሌ ዉስጥ በዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በዘር ማጥፋት ወንጀል የተጠረጠሩ የወያኔ ባለስልጣናትን ለፍርድ ለማቅረብ የሚደረገዉ ጥረት ተጧጡፋል

ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት ጋምቤላ፤ ኦጋዴን፤ ጉራ ፈርዳ፤ ቤንሻንጉል፤ አርባጉጉና አዲስ አባባ ዉስጥ ለፈጸሙት የዘር ማጥራትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠረርጠሪ የሆኑትን የዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣኖች ለአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚደረገዉ ጥረት በአዲስ መልክ ተጧጡፎ መቀጠሉን ሰሜን አዉሮፓ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ኢትዮጵያ ዉስጥ በኦጋዴን ክልል የወያኔ አገዛዝ የሚፈጽመዉን የጦር ወንጀልና የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚያሳዉና በወጣት አብዱላሂ ሁሴን አማካኝነት ከኢትዮጵያ ሾልኮ ከወጣዉ ቪድዮ ጋር ተቀነባብሮ የተሰራዉ ዘጋቢ ፊልም ሲዊድን ዉስጥ በቴሌቪዥን ከቀረበ በኋላ ፊልሙን የተመለከቱ ስዊድናዉያንና ሌሎችም አለም አቀፍ ጠበቆች ጉዳዩን ወደ አለማቀፍ ፍርድ ቤት ለመዉሰድ እስካሁን ድረስ ያልታየ ትልቅ ንቅስቃሴ ጀመረዋል። ወጣት አብዱላሂ ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ በሰጠዉ ቃለመጠይቅ እንደተናገረዉ ፊልሙ በቴሌቪዥን ከተላለፈ በኋላ ሌሎች ብዙ የአገሪቱ ሚዲያዎች ሰፊ ሽፋን አንደሰጡትና ይህንኑ የተከታተሉት ስቴላም የተባሉ የ አይ ሲ ጄ ጠበቃ ጉዳዩን ፍርድ ቤት እንደሚያቀርቡት በሬዲዮ ይፋ አድርገዋል።የስዊድን የጦር ወንጀል ኮሚሽን ፍርድ ቤትም ማስረጃዎችን በመመርመር ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ከወጣት አብዲ ጋራ ቀጦሮ ይዘዋል። ጠበቆቹ ጄኔቫ ካለው አይሲጄ ጋር እና ከሌሎችም የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን ጉዳዩን ወደ አለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ለመውሰድ እንደሚሞክሩ ተናግሯል።

በዚህ “የአምባገነኖች እስረኞች” ተብሎ በተሰየመዉ ፊልም ዉስጥ ልዩ ፖሊስ እየተባለ በሚጠራው ሀይል የተፈጸመ የዘር ማጥፋት ወንጀልን የሚያሳይ መረጃና፣ የክልሉን ፕሬዚዳንት የተቸች አንዲት ሴት በኦበነግ አባልነት ስትፈረጅ የሚያሳይ መረጃ ተካቶበታል ። የክልሉ ፖሊስ ሀላፊው በእስር ላይ የሚገኙትን ሴቶች በመድፈር ብዙ ህጻናት በእስር ቤት ውስጥ መወለዳቸውን በፖሊሶች በራሳቸው ሲነገር የሚያሳይ መረጃም በፊልሙ ዉስጥ መካተቱትንና ፊልሙ ከዚህ በፊት በኢሳት ቴሌቪዥን ቀርቦ በታየዉ ቢድዮ ዉስጥ ያልተካተቱ መረጃዎችን ማቀፉን ወጣት አብዱላሂ ገልጿል።
ኦጋዴን ዉስጥ የሚፈጸመዉን ግፍ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየዉን ፍልምና ፊልሙ ወንጀለኞቹን ለፍርድ በማቅረብ በኩል ያለዉን ፋይዳ አስመልክቶ ኢሳት ቴሌዥንና ሬድዮ ያናገራቸዉ የአለማቀፍ የህግ ባለሙያዎች ኮሚሽን በእንግሊዝኛ ኮሚሽነር የሆኑት ስቴላ ጋርደ ለኢሳት እንደገለጹት የወንጀሉን ፈጻሚዎች ወደ ፍርድ ለማቅርብ የሚችሉትን ሁሉ እንደሚጥሩ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የአለማቀፍ ወንጀል ( ICC) ፈራሚ አገር ባለመሆኗ ማስረጃውን በቀጥታ ለፍርድ ቤቱ መላክ እንደማይቻል የገለጹት ኪሚሽነር ጋርደ፣ ይሁን እንጅ ሰቆቃን ለመከላከል የተቋቋመው ኮሚቴ ( Committe Against Torture) ፈራሚ አገር በመሆኗ ጉዳዩን በዚሁ በኩል ለመከታተል እና የስዊድን ፖሊስ ምርመራ ጀምሮ እርምጃ ለመውሰድ እንዲችሉ ጥረት እንደሚያደርጉ ለኢሳት ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰብአዊ መብት ኮሚቴ እነዚህን ማስረጃዎች እንዲያገኙ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። የኖርዌይ የቴሌቪዥን ጣቢያም ፊልሙን በቅርቡ ያሰራጫል ተብሎ ይጠበቃል። ፊልሙ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በተለያዩ አለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀን ይቀርባል።

## አዲሱ ለገሰ አራት ረዳት ሚኒስትሮች ተመዱለት

እንደ አሮጌ መኪና በነጋ በጠባ ጥገና የሚያስፈልገዉ የባዕዴኑ አዲሱ ለገሰ በሚኒስቴር ማዕረግ በሚሰራበት ቦታ ላይ ረዳት አንዲሆኑት አራት ምክትል ሚኒስቴሮች የተመደቡለት መሆኑን ኢህአዴግ ዉስጥ የሚገኙ ዉስጥ አዋቂ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የወያኔ/ኢሕአዴግ ካድሬዎችን ለማሰልጠን የተገነባውን የፖለቲካ ማሠልጠኛ ተቋም በሚኒስቴር ማዕረግ የሚመራዉ አዲሱ ለገሰ የተመደቡለት አራቱ ረዳቶች ከአራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ማለትም ከኦህዴድ፤ ከባዕዴን፤ ከደህዴንና ከህወሃት የተዉጣጡ ናቸዉ። ከአዲስ አበባ በደረሰን ዜና መሰረት ከብአዴን አቶ ለገሰ ቱሉ፣ ከደሕዴን አቶ ወንድሙ ገዛኸኝ፣ ከሕወሓት አቶ ነጋ በርሄ ሲሆኑ፣ ከኦሕዴድ የተወከለውን አመራር ስም ለግዜዉ ማግኘት አልተቻለም።

ይህ ከሰሞኑ የተሰጠዉ የአራት ምክትል ሚኒስቴሮች ሹመት የወያኔ አገዛዝ ባለፉት ጥቂት አመታት በተለያዩ የስልጣን መወቅሮች ላይ የሚሰጣቸዉ ሹመቶች እጅግ በጣም ግራ የሚያጋቡና ግለሰቦችን ለማስደስት ብቻ ለይስሙላ የሚሰጡ ሹመቶች ናቸዉ የሚሉ ብዙ ተቺዎች ከየአቅጣጫዉ ብቅ ማለት በጀመሩበት ወቅት መሰጠቱ ትችቱን ይበልጥ ተዓማኒ አድርጎታል። ይህ በዋና ላይ ምክትል በምክትል ላይም ሌላ ምክትል የመሾም አዲስ አሰራር በተደጋጋሚ መታየት የጀመረዉ ከመለስ ዜናዊ መሞት በኋላ ሲሆን የመለስን ሞት ተከትሎ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን ቦታ ሲረከብ በመለስ ዘመን ያልነበሩ አራት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴሮች መሾማቸዉ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ ለኃ/ማሪያም ደሳለኝም በአማካሪ ስም አራት ሰዎች መሸማቸዉ የሚታወስ ነዉ።

## አዲስ አበባ ኗሪዎቿን ዉኃ ማጠጣት ተሳናት

የአፍሪካ መዲናና የኢትዮጵያ የልማት ማዕከል መሆኗ የሚነገርላት አዲስ አበባ በከፍተኛ የዉኃ እጦት እየተሰቃየች መሆኗንና ከ35 በመቶ በላይ የሚሆኑ የከተማዋ ነዋሪዎች የሚጠጣ ዉኃ አጥተዉ እንደሚሰቃዩ የወያኔዉ ጠቅላይ ሚኒስቴር በራሱ አንደበት ተናገረ። ኃይለማርያም ደሳለኝ በቅርቡ አዲስ አበባ ዉስጥ የውኃ ቀለም አይቶ የማያውቅ ህዝብ አለ ወይ ተብሎ የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ በተናገረዉ መሰረት 20 በመቶ የሚሆነው አዲስ አበባ ነዋሪ (ከ600 ሺ ሰዉ በላይ) ዉኃ የሚያገኘዉ በሳምንት ለአምስት ቀናት ብቻ ሲሆን 15 በመቶ የሚሆነዉ የአዲስ አበባ ነዋሪ (ከ450 ሺ ሰዉ በላይ) ደግሞ ዉኃ የሚያገኘዉ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ነዉ።

በብዙ አፍሪካ አገሮች የተካሄደ ጥናታዊ መረጃ እንደሚያመለክተዉ በአብዛኛው የአፍሪካ ዋና ዋና ከተሞች ዉስጥ ያለዉ የውሀ አቅርቦት ከ75 እስከ 99 በመቶ የሚሆነዉን ነዋሪ የዉኃ ፍጆታ እንደሚያረካ የታወቀ ሲሆን የአፍሪካ መዲና እየተባለች በምትጠራዋ አዲስ አበባ ዉስጥ ግን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ህዝብ በየቀኑ የዉኃ አገልግሎት አለማግኘቱ ኢትዮጵያ በአመት 11 በመቶ እያደገች ነዉ እየተባለ የሚነገዉን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ጥያቄ ዉስጥ ከትቶታል። አዲስ አበባን በመሰለ አለም አቀፍ ከተማ ዉስጥ ይህንን የመሰለ ከፍተኛ የዉኃ ችግር የሚታይ ከሆነ ከመንግስትም ሆነ ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ እይታ ዉጭ የሆኑት የአገሪቱ የገጠር አካባቢዎች ምን ያህል በዉኃ እጥረት እንደሚሰቃዩ መገመት አያዳግትም ሲሉ ይህንን ዜና አጠናቅረዉ የላኩልን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ተናግረዋል።

## አለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ኢትዮጵያ የሰቆቃ ደሴት ናት አለ

“ሂዩማን ራይት ዋች” በሚል የአንግሊዝኛ ምህጻረ ቃል የሚጠራዉ አለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኘዉ ማዕከላዊ እስር ቤት ሰላማዊ ዜጎች (ጋዜጠኞች፤ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፤ ወጣቶችና ባጠቃላይ ስርአቱን የሚቃወሙ ዜጎች) ይህ ነዉ ተብሎ ሊነገር የማይችል ሰቆቃ የሚፈጸምበት ቦታ ነዉ በማለት የወያኔ አገዛዝ በሰዉ ልጆች መብት ላይ የሚፈጽመዉን በደል ለአለም ህዝብ እንደገና ይፋ አደረገ። “እነሱ የሚፈልጉት ያሰሩት ሰዉ ሲናዘዝ ማየት ብቻ ነዉ” የአዲስ አበባዉ ማዕከላዊ እስር ቤት የሰቆቃና ሰላማዊ ዜጎችን የማሰቃያ ቦታ ነዉ በሚል መሪ ቃል በ70 ገጾች ታትሞ በወጣዉ የድርጅቱ ሪፖርት ላይ ከ35 በላይ ማዕከላዊ እስር ቤት ታስረዉ የወያኔን ግፍና መከራ በአይናቸዉ ያዩና ሰቆቃ የተፈፀማባቸዉ የቀድሞ እስረኞች የምስክርነት ቃል ተካትቶበታል።

የሂዩማን ራይት ዋች የአፍሪካ ዘርፍ ተጠባባቂ ዳይረክተር የሆኑት ወይዘሮ ሌዝሊ ሌፍኮ የኢትዮጵያ ባለስልጣኖች ሰላማዊ ዜጎችን አስረዉ ለማናዘዝ የሚያደርጉት ድብደባና የሚፈጽሙት ሰቆቃ እንኳን በጋዜጠኞችና በተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ላይ በጦር ወንጀለኞች ላይም ሊፈጸም የማይገባ ወንጀል ነዉና አለም ይህንን አይነት በደል ህገ መንግስታዊ መብታቸዉን ተጠቅመዉ ሀሳባቸዉን በገለጹ ዜጎች ላይ ሲደርስ ዝም ብሎ መመልከት የለበትም ብለዋል። ማዕከላዊ እስር ቤት ዉስጥ የሚደረገዉ ምርመራ እስረኞችን የሚደበድብ፤ እስረኞች ዉስጥ እግራቸዉን ከተገረፉ በኋላ ለብዙ ሰዐታት በእግራቸዉ እንዲቆሙ የሚያደርግና አጥንት የሚሰነጥቅና የዘረኝነት ይዘት ያላቸዉ የቃላት ዉርጅብኝም እንደሚያጠቃልል ወይዘሮዋ የተናገሩ ሲሆን አንድ ከኦሮሚያ ክልል ተወስዶ የታሰረ ተማሪ እንደተናገረዉ ምግቡን ሲበላ ጭምር እግሩን እንደሚታሰርና እጅና እገሩን ታስሮ ለቀናት በጨለማ ቤት ዉስጥ እንደተጣለ ተናግሯል።

## አዲስ አበባ ዉስጥ ቦምብ ፈንድቶ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሌላኛው ፍንዳታው ከመድረሱ ከሁለት ሰዓታት በፊት የደረሰ መሆኑን ግብረ ኃይሉ ማረጋገጡን አስረድቷል፡፡ ከሶማሊያውያኑ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው የተባሉ ሦስት ተጠርጣሪዎችና የቤቱ አከራይ በቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራ እየተካሄባቸው መሆኑንም ግብረ ኃይሉ አክሎ ገልጿል፡፡

የወያኔ አገዛዝ የሶማሊያን ግዛትዘልቆ አየገባ በሚፈጽመዉ ጥቃት የተነሳ ኢትዮጵያ ለአመታት ለአልሸባብና ሌሎችም አክራሪ ኃይልች የሽብር ጥቃት የተጋለጠች መሆኗ የሚታወቅ ሲሆን በላፈዉ ወር ኬንያ ናይሮቢ ዉስጥ ለደረሰዉ የሽብር ጥቃት አልሸባብ ሀለፊነት ከወሰደ በኋላ ግን ኢትዮጵያ የሚቀጥለዉ የአልሸባብ ጥቃት ሰለባ ትሆናለች የሚል ከፍጠኛ ፍራቻ አንዳለ ብዙዎች ተናግረዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ቦሌ ዉስጥ እንደዚያ አይነት ከፍተኛ የቦምብ ፍንዳታ ደርሶ ፖሊስ አደጋዉ ወደ ደረሰበት ቦታ የመጣዉ ከ30 ደቂቃ ቆይታ በኋላ መሆኑን የገለጹት የአካባበዉ ነዋሪዎች ስጋታቸዉን ገልጸዋል። እንደ ነዋሪዎቹ አባባል አደጋዉ ደረሰዉ በተወሰነ ቦታ መሆኑና ተጠርጣሪዎቹም ወዲያዉ ስለሞቱ ነዉ አንጂ እንደ ኬንያው ዌስትጌት ጥቃት ቢሆን ኖሮ ፖሊስ የሚደርሰዉ ብዙ ሊተርፍ የሚችል ሰዉ ከሞተ በኋላ ነበር በማለት ብዙ የአካባቢዉ ነዋሪዎች በፖሊስ ላይ ያላቸዉን ስጋት ገልጸዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የሞኝ ዘፈን አሁንም አሁንም አበብዬ. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ለተጨፈጨፉት ሃያ አምስት ሰላማዊ ኢትዮጵያዉያንስ ማን ይዘንላቸዉ፤ ማንስ ሞታችሁ ሞቴ ነዉ ይበላቸዉ? ወይስ ወያኔና ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የሚያሳስባቸዉና የሚያሳዝናቸዉ አገር ዉስጥ እነሱ የሚጨፈጭፉት ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ጎረቤት አገር ዉስጥ የሚሞተዉ ሰዉ ብቻ ነዉ!

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሐይማኖት ተቋሞች የሚያነሱት ጥያቄ የፖለቲካ ጥያቄ ነዉና መንግስት የሚሰጠዉ ምላሽም የፖለቲካ ምላሽ ነዉ ብሏል። መቼም እንዲህ አይነቱ ንግግር በህዝብና በአገር ላይ የሚደረግ ሽሙጥና ስድብ ነዉ እንጂ ከአገር መሪ የሚጠበቅ አስተያየት አይደለም። ለዚህም ይመስለናል ባለፈዉ አመት መለስ ዜናዊ ሞቶ ኃ/ማሪያም ብቅ ሲል የኢትዮጵያ ህዘብ "የዘንድሮዉ ሐምሌ ምንኛ ቅጥ አጣ ተሳዳቢዉ ሲሄድ አሽሟጣጩ መጣ" ብሎ የተረተዉ። መለስ ዜናዊ ሃያ አንድ አመት ሙሉ ህዝብና አገር እንደሰደበ ተገላገልነዉ፤ አሁን ደግሞ እሱን የተካዉ ሰዉ እስከመቼ ይሆን እያሽሟጠጠ የሚኖረዉ? ደግሞስ የሐይማኖት ተቋሞች ለሚያነሱት ጥያቄ ያለን መልስ የፖለቲካ መልስ ነዉ ሲባል እየተላለፈ ያለዉ መልዕክት አናስራለን ነዉ? እንቆነጥጣለን ነዉ ወይስ እንገላለን ነዉ? ኃ/ማሪያምም ሆነ ጌቶቹ ከዚህ የተለየ መልስ ካላቸዉ ይንገሩን። እስሩ፤ ዱላዉና ግድያዉማ ድሮም የምናዉቃቸዉ የወያኔ የቀን ከቀን ድራማዎች ናቸዉ።

ወያኔ የዛሬ ሃያ አመት ሰላማዊ ዜጎችን ይገድል ነበር ዛሬም ይገድላል፤ አዲስ አበባ ዉስጥ አንዴ ቦምብ እያፈነዳ ሌላ ግዜ ደግሞ እራሱ መሬት ቆፍሮ የቀበረዉን ፈንጂ የቴሌቪዥን ካሜራዉን ደርድሮ እራሱ እያወጣዉ በተቃዋሚዎች ላይ እያሳበበ ኖሯል፤ ዛሬም ከዚህ ርካሽ ተግባሩ አልተቆጠበም። ዛሬማ ጭራሽ ኢትዮጵያ ዉስጥ ነጻነትና ዲሞክራሲ እያለ የጮኸዉን ሁሉ ግንቦት 7 ነህ እያለ እስር ቤት እየወረወረ ነዉ። ባለፈዉ አመት መለስ ዜናዊን የተካዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝም እንደዚሁ ነዉ። እንዳዉም ኃ/ማሪያም ሂድ ሲሉት የሚሄድ፤ ተናገር ሲሉት የሚናገር፤ ዝም በል ሲሉት ደግሞ አፉን ዘግቶ የሚቀመጥ ተንቀሳቃሽ ዕቃ ነዉ። ይህ ሰዉ በጌቶቹ እየታዘዘ ከአመታት በፊት በክልል ደረጃ በሲዳማ ህዝብ ላይ የፈጸመዉን ይህ ነዉ የማይባል በደል ዛሬ በብሔራዊ ደረጃ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየፈጸመ ነዉ። ኃ/ማሪያም ባለፈዉ ዐርብ መስከረም 26 ቀን በየሳምንቱ የሚደረገዉ ሰልፍ ሰለቸኝ እያለ በህዝብና በአገር ላይ አሽማጥጧል፤ ይህ ማንነታችን ያልገባዉ ሰዉ እሱና ጌቶቹ የማምለክ መብቴ ይከበር ያለዉን አክራሪ፤ መብቴና ነጻነቴ ይከበር ያለዉን ሽብርተኛ፤ ፍትህና ዲሞክራሲ ናፈቀኝ ያለዉን ደግሞ ግንቦት ሰባት ናችሁ እያሉ የሞኝ ዘፈን ሲዘፍኑ የኢትዮጵያ ህዝብ መሰልቸት ብቻ ሳይሆን ቋቅ እንዳለዉ ማወቅ አለበት። ሞኝን ሞኝ ብለን የምንጠራዉ አንድን ነገር ሺ ግዜ ስለሚደጋግም ወይም ዘፈኑ አሁንም አሁንም አበብዬ ስለሆነ ነዉ። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ሞኝ ብለን እንዳንጠራዉ የሚፈልግ ከሆነ ይህንን ከወያኔ መዝገብ እየተዋሰ የሚዘፍንብንን "ሁል ግዜ አበብዬ" ዘፈኑን ማቆም አለበት። አለዚያ "ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" ነዉና ግንቦት ሰባትና የኢትዮጵያ የነጻነት ኃይሎች ኃ/ማሪያምንና ዘረኞቹን የወያኔ መሪዎች ጠራርገዉ አራት ኪሎንና የሚኒልክ ቤ/መንግስትን የሚያጸዱበትን ግዜ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በህልሙ ሳይሆን በዉኑ ያየዋል።

---

## ዘመነ ፍዳው እንዲያጥር ለምትፈልጉ ወገኖች ሁሉ! (ክፍል 3 የመጨሻ ክፍል )

**(ይነጋል በላቸው)**

4. ግሩም ሲናገር የሰማሁት አንድ ቁም ነገር አለ:: ለድረ ገፆች የሚልካቸውን አንገብጋቢ ጉዳዮች የማያወጡና በሌላ በኩል ግን ሌላ አዘናጊ ፍሬ ፈርስኪ የሚለጥፉ ዘበናይ ድረገፆች መኖራቸውን በቁጭት ጠቁሟል፤ ይህን እኔም በሚገባ አውቃለሁ - ሊያውም በአግራሞት:: አሁን በዚህ በጭንቅ ቀን በነዚህ ዓላማቸው የተለያዩ - ምናልባትም የወያኔ ተቀጥላ ሊሆኑ በሚችሉ የሚዲያ ተቋማት ላይ መዝመቱ ጊዜንና ጉልበትን በከንቱ ማባከን ስለሚሆን እንጂ በብዙዎቹ ላይ ብዙ ነገር መናገር በተቻለ ነበር:: ለጊዜው ግን ቆም ብለው ቀልብ እንዲገዙ እንመክራቸዋለን - ለቀለብ ብለው ቀልብን አጥተዋልና:: ሰው በወደደው እንደሚቆርብ እነዚህ ጤናማነታቸው የሚያጠራጥር ሚዲያዎችም የፈለጉትን የመሆን መብት አላቸው:: ቢችሉ ግን የሀገሪቱንና የሕዝቡን ችግር ቢያሳውቁ ለነሱም የወደፊት ግለ-ታሪክ ይበጃል፤ ከተወቃሽነት ከመዳን አልፈው ትውልዳቸው በነሱ የአሁን ቅሌት አንገቱን ከመድፋት ይድናል፤ ትውልድን አንገት ማስደፋት በነመለስ ይብቃ:: አለበለዚያ ሕዝቡ ያላሳከከውን የሚያኩለት ከሆነና የጠላቱ ተባባሪዎች እንደሆኑ መቀጠል ከፈለጉ የሚያግዳቸው የለምና በጌታቸው አነጋገር ‹መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው›(ልብ በሉ - የመለስ ጉልበትና የዕብሪት ምንጭ ከምንም ያላዳነውና ቡችሎቹንም ከምንም የማያድናቸው ሰው ሠራሽ ጠመንጃ ነው - የኛ ግን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለምሥኪኖች ሊዘረጋላቸው ያዘጋጀው የመጨረሻው ዱላ መለኮታዊ ወገናዊነት ነው)፤ መታወቅ ያለበት አንድ ዋና ነገር በሚዲያም ሆነ በሌላ መንገድ ከወያኔ ጋር የሚተባበሩና የጭቁኖችን የነጻነት ቀን በማዘግየት ረገድ አሉታዊ ሚና የሚጫወቱ ወገኖችም ቢሆኑ ቢያንስ ቢያንስ እየቆዩ ከሚሸነቁጣቸው የኅሊና ፍርድ ሊያመልጡ የማይችሉ መሆናቸው ነው - ይህን ይረዱ፡- ዛሬ ነጭን ጥቁር፣ ጥቁርን ነጭ ማለት ይቻላል - ቀላልም ነው፤ ነገር ግን እንዲህ የማይባልበትም ቀን መምጣቱን ሁሉም ሊገነዘብና ራሱን በማስተካከያው ቀን ሊያስተካክል ይጠበቅበታል - ያም ቀን ዛሬና አሁን ነው:: በኋላ ማፈር አለ፤ በኋላ መደበቅ አለ፤ በኋላ መፍራትም አለ፤ በኋላ ለ‹በኋላ› ለራሱ የመትረፍ ዕድልን አለማግኘትም አለ - የመመለሻ ጊዜዎች ገደብ እንዳላቸው አለማወቅ ግብዝነት ነው - The door of repentance and atonement is not indefinitely open to any one in any given circumstance. There are times during which golden opportunities are denied if once missed. Remember what Jesus said with regard to Judas' betrayal after he sold Him for thirty pieces of silver. ቅድስት ኢትዮጵያን በሚመከት የመመለሻው ወቅት አሁንና አሁን ብቻ ይመስለኛል - አይምሰልህ የምትል በሚያዋጣህ የጥፋት ጎዳና መትመምህን ቀጥል - የጌታህን ቃል በድጋሚ ላስታውስህና ‹መንገድህን ጨርቅ ያድርግልህ› ልበልህ፤ አሽሙረኛው መለስ በተቃዋሚዎች ላይ ሲዘባበት ‹እናንተ እኛን ለመዋጋት ያብቃችሁ እንጂ ቁምጣ እናሰፋላችኋለን› ያለውን እዚህ መድገም ነውር ነው - እንዲህስ የትምና እንዲህም አይባልም - የቀደመውንም ለቀልድ እንጂ ለምር አላልኩትም - መጽሐፉ ‹ትዕቢትስ ፀሩ ለክርስቶስ› ይላልና በምንም ነገር መመፃደቅ ግብዝነት ነው - ደግሞም ቅዱሱ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- ‹ኢይድኅን ንጉሥ በብዝኃ ሠራዊቱ - ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም›:: መለስ በግብዝነቱና በሰይጣናዊ ዕውቀቱ ተኅዳበት - ተቀሰፈበት - እንጂ አልተጠቀመበትም:: የሚሠሩትን የማያውቁት ወያኔዊና ወያኔ-ቀመስ ድረገፆችም ይሁኑ ሌሎች ማስተዋል የተሣናቸው ኃይሎች ሁሉም ነገር እንዲህ እንደደፈረሰ የሚቀር ከመሰላቸው ተሳስተዋል:: በዚያም ላይ የኢትዮጵያ ችግር ሚዲያ ኖረም አልኖረም መወገዱ አይቀርም፤ ትርፉ ትዝብት ብቻ ነው እንጂ የታሪክን እሽክርክሪት በሬዲዮ ጋጋታም ይሁን በቴሌቪዥን ጩኸት የነጻነት ባቡሩ እንዳይመጣ ለሴከንድ አናዘገየውም ወይም ቶሎ እንዲደርስ አናፈጥነውም፤ የእኔም መጣጥፎች እንዲሁ ናቸው - ለመተንፈስ ብቻ:: የወያኔ ቲቪና ተቀጥላው ተቃዋሚ መሰል ድረገፅ ኢትዮጵያ አረንጓዴ በአረንጓዴ ሆናለች፤ ዕድገቱ 333 በመቶ ደረሰ፣ ግሽበቱ ወደ 0.005 ወረደ፤ ኢሕአዴግ በ‹እንከን የለሽ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ› 99.99 ከመቶ በሆነ ውጤት ‹ተቃዋሚዎች›ን በዝረራ አሸነፈ.... ቢባል መሬት ላይ ካለው እውነት ጋር ዐይንና ናጫ ስለሆነ የፈጠጠው ገሃድ እውነት ይህን ውሸት መገንዘብ ለሚፈልግ ሚዛናዊ ሰው ከመገንዘብ አይገታውም - ምድረ ወያኔ አለቃውን እየተከተለ እንደጣቃ በውሸት ቢተረተር፣ ገበሬን ሚሊዮኔር አደረግሁ ተብሎ እየተደሰኮረ በቤቱ ይቀምሰውና ይልሰው ምናምኒት በሌለው ጭቁን ሕዝብ ላይ ቢቀለድ እውነቱ ባለበት ስላለ ሲነጋ ለማፈር ካልሆነ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ አይለውጥም:: ኤፍኤሞቻችንም በወሲብ ወሬ፣ በጫትና በሀሽሽ የምርቃና አይሬ ዘፈን፣ በድሪያና እንቶፈንቶ ቱማታ እንዲሁም በአርሰናልና ቼልሲ ባዕዳን የእግር ኳስ ጨዋታ ትንታኔ በተለይ ወጣቱን ሲያደነቁሩት ውለው ሲያደነቁሩት ቢያድሩም አሁንም አስደንጋጩ እውነት ካለበት አንድ ጋት እንኳን ወደፊት ንቅንቅ አይልም:: ኮብል ስቶንና አስፋልትም ግፋ ቢል ከጭቃ ይገላግሉን እንደሆነ እንጂ እንደእሳት የሚጋረፍን ርሀብ ለማስታገስ ወደ ሆድ ጠብ የሚል ነገር አያስገኙም - ሊያውም በባቡር መስመር ዝርጋታ ምክንያት በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ትርምስመሷ ስለወጣ ጉዟችን ሁሉ እንደጉዞ ፍትሃት ሆኖአል - በአሁኑ ሰዓት አዲስ አበባን አለማየት ነው:: ሕንጻውና ፋብሪካውም ለወያኔዎችና ለነሱው ጥገኛ ኢንቬስተሮች የአላግባብ ብልጽግና ምንጭ ከመሆን በዘለለ ጭቁኖችን አልጠቀሙም - የተመሰቃቀለና ለመግለጽም የሚያዳግት ሁኔታ ነው ያለው በሀገራችን:: ... በነገራችን ላይ ... አይ ይቅርብኝ ተውኩት::

ለማንኛውም ልብ ያለው ልብ ይበል:: ልብ ብሎም ብዙም ሳይረፈድ ወደኅሊናቀው ይመለስ:: የሚታየኝን አላውቅም - ግን የነጻነት ቀን በእጅጉ መቅረቧ ይሰማኛል፤ ብዙ ተሰቃይተናልና ይገባናልም:: እምልላችኋለሁ - ከኅያው እግዚአብሔር በስተቀር የምተማመነው ሌላ ምድራዊ ኃይል በኢትዮጵያ ሕዋ ውስጥ በምናብ እያየሁ አይደለም እንዲህ በልበ ሙሉነት ነጻነታችን ቀርባለች የምለው - እርሱን ያመኑ አያፍሩም:: በእስካሁኑ አካሄዳችን በሰው መተማመን ብዙ የኅሊና ቀውስ ውስጥ እንደከተተኝ ስለምረዳ በሰው መተማመኔን እርግፍ አድርጌ ትቻለሁ - ይህንንም ስል እግዚአብሔር ራሱ ወርዶ አንድን ሕዝብን ነጻ እንደማያወጣ አውቃለሁ - በመረጣቸው ሥራውን ይሠራል እንጂ::

ሰው በተለያዩ ምክንያት ከአውነት መንገድ ሊወጣ ይችላል - እስከወዲያኛው ጭንቅላቱን ለሆዱ ወይም ለሸውራራ አስተሳሰብና ለጠማማ እምነት ካዋለ በቋሚነት እንደዋሸ ይኖራል - እውነትን ለመረዳት ተወነባብዶ ወይም እውነታው ከሀሰቱ ተሳክሮበትም ከሆነ በማስረጃና መረጃ የተጠናከረ የጠራ ግንዛቤ እስኪይዝ ድረስ ላልተወሰነ ጊዜ የውሸት ሰለባ እንደሆነ ሊቆይና ወደእውነቱ ሊመለስ ይችላል - ያኔ እንደገና ተወለደ:: በዋናነት በዘረኝነት ልክፍት፣ በይሉኝታ፣ ከሰው ጋር ላለመቀያየም፣ በ‹ከነገሩ ጦም እደሩ› የሰነፎች ይትበሃል፣ በትውውቅና በመሳሰለው ሰዎች ዐይናቸውን ጋርደው ከእውነት አደባባይ በመሠወር ወደሀሰት ሸርንቁላ ሊወተፉ ይችላሉ:: ... ለነገሩ አሁን እኔን በዚህ ጉዳይ ምን ጥልቅ አደረገኝ! አሃ፣ ያገባኛል እንጂ:: እናሳ? ምን ላደርግ እችላለሁ? ማድረግ የምችለው - እግዚአብሔር ከ‹ጨለማ ወደ ብርሃን ያውጣቸው› ብሎ መጸለይ ነው:: እኔስ የትኛው ውስጥ ነው የምኖር? ከግምት ባለፈ አላውቅም:: ግን የሚቃወሙኝ ሊጸልዩልኝ ይችላሉ - ‹ከጨለማ ወደ ብርሃን ያውጣህ› ብለው:: እንጸላለይና መሀል መንገድ ላይ እንገናኝ:: ያኔ ሰማይና ምድር ይታረቃሉ፤ ያኔ ማንም የማንንም ድቀትና ሞት አይመኝም:: ያኔ የዲያሎስ ቀንድ ይሰበራል - ክንፉም ይረግፋል:: በቃ::